ኦገስት 1, 2023

የተወደዱ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ወላጅ

የልጅዎን ትምህርት ቤት የሚያገለግሉ የአውቶቡሶች መስመር መርሃ ግብር አባሪ ተደርጓል። ይህ መረጃ MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል። እባክዎ ለልጅዎ የተመደበውን ሰዓት፣ በታ እና የአውቶቡስ መስመር ቁጥር ያስተውሉ። አብዛኛዎቹ የአውቶቡስ መስመሮች የተነደፉት ተማሪዎች የት/ቤት አውቶቡስ ለመሣፈር አውራ መንገዶችን እንዳያቋርጡ ተደርጎ ነው። ይህ የአውቶቡስ መስመር መግለጫ "RSO" (በቀኝ በኩል ብቻ) ከአውቶቡስ ማቆሚያ ምልክት ቀጥሎ ተገልጿል። ወላጆች ለልጆቻቸው ደህንነት ስጋት እንዳይሆን ሌላ የአውቶቡስ ማቆሚያ ለመጠቀም ብለው መንገድ በማቋረጥ ሌላ ፌርማታ እንዲሄዱ መፍቀድ የለባቸውም። መንገድ ሳያቋርጡ በእነርሱ በኩል ምንም የአውቶቡስ ማቆሚያ የሌለ ከሆነ ወላጆች የዴፖ ማኔጀር ማነጋገር አለባቸው የት/ቤት አውቶቡስ መስመር ቁጥሮች በእያንዳንዱ አውቶቡስ በጎን መስኮት ላይ ተለጥፎ ይታያል። ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ለእርስዎ የትራንስፖርት መናኸሪያ ቅርንጫፍ (transportation depot) መቅረብ ይኖርባቸዋል። ከት/ቤትዎ ወይም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በይነመረብ ላይ ስለ ኣካባቢዎ ት/ቤት የትራንስፖርት ምድብ (transportation cluster) መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

ከአካባቢያቸው ት/ቤት አንድ (1) ማይል የበለጠ ርቀው ለሚኖሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የት/ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ከትምህርት ቤቱ 1 ማይል ብቻ ርቀት ላይ የምትኖሩ ከሆነ እና ስለ አካባቢያችሁ በወጣው ዝርዝር ላይ የት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ካላገኙ፣ ልጅዎ የመጓጓዣ አገልግሎት ለማግኘት ብቁ አይደለ(ች)ም። ቀደም ሲል ተመድበው የነበሩ የአውቶቡስ መስመር ማቆሚያዎች ተወግደዋል ወይም በቁጠባ አብቃቅቶ የመጠቀም ሥራ ላይ ተመድበዋል። በተማሪዎች እና በወላጆች ላይ የሚደርሱ የማይመቹ ሁኔታዎችን ለመቀነስ እና ምክንያታዊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የተቻለ ጥረት ሁሉ ይደረጋል። በድጋፍ የተገኘ በጀት ዶላርን መቆጠብ ለመማሪያ ክፍሎች ተጨማሪ መገልገያዎችን ለማቅረብ ይረዳል።

*ተገቢ የሆነ የተማሪ ባህሪ ለሁሉም ሰው ደህንነት እና ምቾት አስፈላጊ ነው። ይህንን መልእክት ለማጠናከር ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ዘወትር ስለ ባህሪ እንዲወያዩ ይበረታታሉ። ሁሉም ተማሪዎች "ህግ እያከበሩ መጓዝ/Ride by the Rules.።" በተሰኘ ዘመቻ ላይ የተዘረዘሩትን ህጎች መከተል እንደሚኖርባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው። በዚህ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይህንን በይነመረብ ይጎብኙ:* https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/rules/

ወላጆች ልጆቻቸው እስከ አውቶቡስ መቆሚያ በታ ሲመጡ፣ በአውቶቡስ መቆሚያ ላይ ሲጠባበቁ፣ እና አውቶቡስ ከሚቆምበት በታ ወርደው ወደቤት በሚመለሱበት ጊዜ ሁሉ ሀላፊነት አለባቸው።ልጆች ከተመደበው የት/ቤት አውቶቡስ መሳፈርያ ሰአት ቢያንስ ከአምስት ደቂቃ በፊት በታው ላይ መድረስ አለባቸው። ወላጆች ከሰአት በኋላ የት/ቤት አውቶቡስ ፌርማታ ላይ ልጆቻቸው ከአውቶቡሱ እንደወረዱ ወዲያውኑ የመቀበል ኃላፊነት አለባቸው፥ እንዲሁም የት/ቤት አውቶቡስ መቆሚያ ላይ መጠበቅና ተንከባካቢ ወይም ሌላ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው ልጆቹን በደህና ወደ ቤት ወይም ወደ ሕፃናት መንከባከቢያ

እንዲሸኝ የማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን ከት/ቤት አውቶቡስ መውረድ ያለባቸው የት በታ እንደሆነ ማስተማር እና የአውቶቡስ ፌርማታውን ወይም መሬት ላይ የሚገኙ ምልክቶችን ልዩ ምልክቶች እንዲያውቁ ማድረግ አለባቸው። ስለዚህ በመጀመሪያ ቀን ልጆች በት/ቤት አውቶቡስ ከመሳፈራቸው በፊት ልጆቹ የት እንደሚወርዱ ፌርማታውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ እንዳለብዎት እባክዎን ያስተውሉ፡ የአውቶቡስ ኦፕሬተሮች በአንድ ቀን ውስጥ  እያንዳንዱን ልጅ የሚረከብ ሰው ማን እንደሆነ ለይተው አያውቁም፣ እያንዳንዱንም ልጅ ከአንድ አዋቂ  ሰው ጋር ማገናኘት አይችሉም።

ተማሪዎች ከአውቶቡስ ሲወርዱ፣ ሙሉ በሙሉ በወላጅ ወይም በተንከባካቢው ቁጥጥር ናቸው፣ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ ከሌለ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ብቻቸውን እንደሚሆኑ መዘንጋት የለበትም።እባክዎን ልጆችዎ ወላጅ ካላገኙ ከት/ቤት አውቶቡስ ከመውረዳቸው በፊት በትክክል የት ፌርማታ ላይ እንደሚወርዱ እና የአውቶቡስ ኦፕሬተሩን ወዲያውኑ ማሳወቅ እንዳለባቸው በማረጋገጥ ወይም በአውቶቡስ ማቆሚያ ላይ በመደበኛነት የሚጠብቃቸው ሌላ ሰው ከሌለ ራሳቸውን ችለው የሚወርዱበትን ሁኔታ በትክክል ያሰልጥኗቸው።አውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ሁኔታውን ካወቀ(ች)፣ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ት/ቤት ይመልሳል/ትመልሳለች፣ ወይም የተማሪው(ዋ)ን ደህንነት ለመጠበቅ ሌላ እርምጃ ይወስዳል/ትወስዳለች።

ብዙውን ጊዜ በት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ልጅዎን የሚጠብቁት እርስዎ ከሆኑ እና የተወሰነ ቀን ላይ ማድረግ ካልቻሉ፣ ከትምህርት ቤት የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ወደ ትምህርት ቤት ደውለው ልጅዎ በአውቶቡስ ከመሣፈር ይልቅ መጥተው እስኪረከቡ ድረስ በትምህርት ቤት እንዲቆይ/እንድትቆይ ይጠይቁ። ይህ ሊደረግ የሚችለው እርስዎ ባልታሰበ ድንገተኛ ምክንያት ከአውቶቡስ መቀበያው በታ ለመድረስ የማይችሉ/የሚዘገዩ ከሆነ ብቻ የሚተገበር የድንገተኛ ሁኔታ እቅድ ነው። አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ዝግጁ እንዲሆኑ የት/ቤቱን ቴሌፎን ቁጥር በእጅ ስልክዎ ወይም በማይለዩት ሌላ ማስታወሻ ላይ መያዝ አለብዎት። እርስዎ ወይም ሌላ ተንከባካቢ በማይገኙበት ከሰአት በኋላ አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ልጅዎ ከታላቅ ወንድም ወይም እህት ጋር ወይም የክፍል ጓደኛ ጋር የመሆን እቅድ እንዲያዘጋጁ ይመከራል። የት/ቤት አውቶቡስ የጊዜ ሠሌዳዎች ግምታዊ ናቸው፥ በትራፊክ መጨናነቅ፣ በአየር ሁኔታ እና በተማሪ ቁጥር ለውጦች ምክንያት ሊቀያየሩ ይችላል፣ ስለሆነም ከመደበኛው የመቀበያ ሰዓት ቀድመው በት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያና ማውረጃ በታ ላይ መገኘት አለብዎት።

ሲሳፈሩ፣ ሲጓዙ እና ከአውቶቡስ ሲወርዱ የደህንነት ደንቦችን መከተል በጣም አስፈላጊ ነው። የደህንነት ህጎችን ከልጅዎ ጋር ሆነው መገምገም የአውቶቡስ ጉዞ ደህንነትን ለማረጋገጥ ያግዛል።

<u>ዋና ዋና ነጥቦች</u>

ከሰአት በኋላ ከት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ወደ ቤት ሲሄድ/ስትሄድ ልጅዎ በአዋቂዎች ቁጥጥር እንዲሆን ከፈለጉ፣ ያ መደረጉን ማረጋገጥ አለብዎት። ተማሪው(ዋ) ከአውቶቡስ ከወረደ(ች) በኋላ፣ክትትል ማድረግ የሚችሉት እርስዎ ብቻ ነዎት። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አውቶቡስ ከወጡ በኋላ ክትትል ስለሚያስፈልጋቸው የሚከተለውን እንመክራለን።

- አውቶቡሱ በማንኛውም ቀን ቀደም ብሎ ሊመጣ ስለሚችል እርስዎ ወይም ሌላ ተንከባካቢ/ተቀባይ ሰው ከመደበኛው የመቀበያ ሰዓት በፊት በአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ ላይ እንደምትገኙ ያቅዱ።

- በሆነ ቀን እርስዎ የማይገኙ ከሆነ ልጅዎን አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ ተገኝቶ የሚቀበል የተለመደ አዋቂ ሰው እንደሚገኝ በቅድሚያ ያቅዱ።

- ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠመዎት እና ወደ አውቶቡስ ማቆሚያው በጊዜ መድረስ የማይችሉ ከሆነ <u>ተማሪዎች ከት/ቤት ከመሰናበታቸው በፊት</u> ወደ ትምህርት ቤት ደውለው ይንገሩ። ይህም ልጅዎ በት/ቤት አውቶቡስ ከመጓዝ ይልቅ እርስዎ መጥተው እስከሚወስዱ(ዷ)ት ትምህርት ቤት እንዲቆይ/እንድትቆይ ያደርጋል። ሊያስፈልግዎት ስለሚችል ሁል ጊዜ የትምህርት ቤቱ የስልክ ቁጥር እንዳለዎት ያረጋግጡ።

- ልጅዎ ከት/ቤት አውቶቡስ የሚወርድበትን/የምትወርድበትን ትክክለኛውን የአውቶብስ ፌርማታ እንደሚያውቅ/እንደምታውቅ እና በሌላ ማቆሚያ ላይ ከአውቶቡሱ እንደማይወርድ/እንደማትወርድ ማወቁ(ቋ)ን እርግጠኛ ይሁኑ።

- ከልጅዎ ጋር ወደ ቤት የሚሄድ ትልቅ ተማሪ "ጓደኛ" ያዘጋጁ፥ ወይም እርስዎ እስከሚወስዱ ድረስ ልጅዎን በቤታቸው እንዲቆይ ይፍቀዱለት። ይህን ሲያቅዱ ከሌላኛው ተማሪ ወላጅ ጋር መነጋገርዎን ያረጋግጡ።

- አንድ ነገር "ትክክል ካልሆነ"፣ ልጅዎ ከአውቶቡስ ከመውረዱ(ዷ) በፊት ለአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) መንገር እንዳለበ(ባ)ት አስረግጠው ይንገሩ። ከሌሎች ነገሮች ሁሉ በተጨማሪ ይህ ሊሆን የሚችለው፥ አብዛኛውን ጊዜ በፌርማታው ላይ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ የማይገኝ ሲሆን፣ መውረጃቸውን በመዘንጋት፣ የሚወርዱበትን ፌርማታ ባለማወቃቸው ወይም በስህተት በሌላ የት/ቤት አውቶቡስ ውስጥ ገብተው ከሆነ ነው።

- ተማሪዎች እንስሳትን፣ አልኮልን፣ ትምባሆን፣ የጦር መሳሪያዎችን (አሻንጉሊት ወይም “የሚመስሉም ቢሆን” መሳሪያዎችን የመሣሰሉ ነገሮችን)፣ ከመስታወት የተሠሩ መጠጫዎች/እቃ መያዣዎችን፣ ወይም ፈንጂዎችን በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ ይዘው መገኘት/ማምጣት የለባቸውም።

የት/ቤት አውቶቡስ ፌርማታዎች በመስቀለኛ መንገድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ተማሪዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ከትራፊክ ርቀው፣ ከአውቶቡስ ማቆሚያው 150 ጫማ ርቀት ላይ መቆም አለባቸው። *በት/ቤት አውቶብስ ፌርማታዎች ላይ ወላጆች ዲሲፕሊን እና ደህንነትን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።* የት/ቤት አውቶቡሶችን የሚጠብቁ ተማሪዎች ከአየር ሁኔታ ለመጠለል ከፈለጉ በመኪና ፓርኮች እና ጋራዥ ውስጥ መቆም ይችላሉ። ይህ ተቀባይነት የሚኖረው፦ (1) መንገድ የማያስቀይር ከሆነ፣ (2) ለአውቶቡሱ የማቆሚያ ብዛት የማይጨምር ከሆነ፣ (3) በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተቀባይነት ካገኘ፣ እና (4) ከመደበኛው ፌርማታ ጋር ተቀራራቢ ቦታ ከሆነ (ልዩ ሁኔታውን የማያ(ታ)ውቅ ተለዋጭ የአውቶቡስ ኦፕሬተር ተማሪዎቹን በቀላሉ ለማግኘት አመቺ ከሆነ) ብቻ ነው። እባክዎን ያስታውሱ፦ የአውቶቡስ ኦፕሬተሮች እንዲያቆሙ

የተፈቀደላቸው በተሰየሙ ፌርማታዎች ላይ ብቻ ስለሆነ ያልተፈቀደላቸው ማቆሚያዎች ላይ እንዲያቆሙ አትጠይቋቸው። MCPS የአውቶቡስ ፌርማታዎችን ቁጥር በመገደብ ከፍተኛ የነዳጅ እና ሌሎች የአሰራር ቁጠባዎች መኖር እንዳለባቸው ይገነዘባል።

ጓደኛ በሚሣፈርበት/በምትሳፈርበት የት/ቤት አውቶቡስ አብሮ ለመሳፈር ወይም ጓደኛ በሚወርድበት/በምትወርድበት ማቆሚያ ላይ አብረው ለመውረድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ፈቃድ ማግኘታቸውን ማስታወሻ ይዘው መምጣት አለባቸው። የተፈቀደላቸው መሆኑን ከታወቀ እና በርእሰመምህሩ ከተፈረመ፣ ተማሪው(ዋ) ለሚሳፈሩበት አውቶብስ ኦፕሬተር ማስታወሻውን መስጠት አለበ(ባ)ት። ብዙውን ጊዜ ይህ አሰራር ሊፈቀድ የሚችለው በት/ቤት አውቶቡስ ቦታ ሲኖር ብቻ ነው።

አመቺ ያልሆነ የአየር ሁኔታ ለሁሉም ሰው ከባድ ችግሮችን ይፈጥራል። በዊንተር ወራትም ሆነ በዝናባማ ቀናት ተጨማሪ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አይቻልም፤ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች ለአየር ሁኔታው ተስማሚ/ተገቢ የሆነ ልብስ መልበስ አለባቸው። በሚያዳልጥ በረዶ እና በበረዶ ክምር ምክንያት አውቶቡሶች ወደተዘጋጀላቸው ፌርማታዎች በጊዜ መድረስ ካልቻሉ፣ ወላጆች ከአውቶቡስ ኦፕሬተሮች ጋር ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ እና በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በተለዋጭ ቦታዎች እንዲሳፈሩ ይበረታታሉ።

ተማሪዎችን ማጓጓዝ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ ከተወጣን ብቻ ነው። ለተማሪ ተሳፋሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ የመጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት የወላጅ እርዳታ እና ትብብር ያስፈልጋል።

ከልብ

Depot Manager

XXX:-xxx

አባሪ